

“መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ሩጫውን ጨርሻለሁ”

2ኛ ጢሞቴዎስ ም 4 ቁ 6-7

# የዶ/ር መንግስቱ ለማ ወርቅነህ አጭር የህይወት ታሪክ

ዶ/ር መንግስቱ ለማ ከአባቱ ከአቶ ለማ ወርቅነህ እና ከ እናቱ ከ ወይዘሮ እልፍነሽ ገ/እግዚአብሄር በ 1952 አ/ም በ አሰላ ከተማ ተወለደ። የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በአሰላ ከተማ ካጠናቀቀ በሁዋላ ፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደብረ ዘይት እርሻ ኮሌጅ በዲፕሎማ ተመርቆ ከ 1972 እስከ 1977 በመንግስት እርሻ የ አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት ገርዴል እርሻ የሰብል ጥበቃ ሃላፊ በመሆን አገሩን አገልግሏል።

ዶ/ር መንግስቱ ለማ ለትምህርት በነበረው ፍቅር ምክንያት በ 1978 አ/ም አለማያ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ በመማር በ 1980 በባችለርስ ዲግሪ በማእረግ ተመርቆ በተማረበት ዩኒቨሲቲ ከ 1981-1984 ባሉት አመታት በማስተማር እና የምርምር ስራ በመሰማራት ምሁራዊ እና ኢትዮጵያዊ ግዴታውን ተወጥቱኣል። በዚህም ጊዜ ከባለቤቱ ከወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገየ ጋር ትዳር መስርቶ የ ሁለት ሴቶች ልጆች አባት ሆኖአል።

ዶ/ር መንግስቱ ለማ በ 1985 ባገኘው የከፍተኛ ትምህርት እድል ወደ አሜሪካ መጥቶ በ 1987 ከኦሬጋን ስቴት ዩኒቨርሲቲ በእጽዋት ሳይንስ የማስተርስ ዲግሪውን አገኘ። በማከታተልም ትምህርቱን በመቀጠል በ 1991 የ ፒ .ች ዲ (ዶክቶሬት) ዲግሪዉን በጀመረው የእጽዋት ሳይንስ አጠናቀቀ።

ዶ/ር መንግስቱ ለማ ከ 1992-1997 በ ሰሜን ዳኮታ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ተቀጥሮ በማስተማር እና በምርምር ስራ በርካታ ወጣቶችን አሰልጥኖአል። ቀጥሎም ከ 1998-1999 ባለው ጊዜ በሚኒሶታ ዲፓርትመንት ኦፍ አግሪካልቸር በ ከፍተኛ ሳይንቲስትነት ተቀጥሮ የሚኒሶታን ህዝብ አገልግሉአል።

ዶ/ር መንግስቱ ለማ በትምህርትም ሆነ በስራ ላይ በቆየባቸው አመታት በርካታ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለሙያ አጋሮቹ እና ለ ዓለም ማቅረብ የቻለ ታላቅ ምሁር ነበር።

ዶ/ር መንግስቱ ለማ በህይወት ዘመኑ ቤተሰቡን የሚወድ፤ ሰው አክባሪ፤ተጨዋች እና ታጋሽ የነበረ ሲሆን በተለይም ለአገሩ እና ለኢትዮጵያ ህዝብ የነበረዉን ፍቅር በ ሙያው ለመግለጽ በዝግጅት ላይ እንዳለ በድንገት ባደረበት ህመም ለ ሰባት ወራት በህክምና ሲረዳ ቆይቶ መጋቢት 13/2002 ከዚህ አለም በ ሞት ተለይቷል። የቀብሩ ስነ ስነ ስርአት በተወለደበት በአሰላ ከተማ ይፈጸማል።

በህመሙ ጊዜ ተገኝታችሁ ላፅናናችሁ ካረፈም በሁዋላ በማንኛዉም መንገድ ለረዳችሁ ሁሉ ባለቤቱ ወ/ሮ ጥሩወርቅ ዘገየ እና ልጆቻቸው ምስጋናቸውን ያቀርባሉ።